# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 91 የካቲት 4 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ወያኔ በለንደን የሚገኘውን የኢትዮጵያን ኢምባሲ በህገወጥ መንገድ ለመሸጥ ሲስማማ ተደረሰበት

ሙሉ ትኩረቱን በገንዘብ ማግበስበስ ስራ ላይ ያዋለው የወያኔው አገዛዝ በእንግሊዝ ሃገር ሎንዶን ከተማ የሚገኘዉን የኢትዮጵያን ኤምባሲ ህንጻ በመሸጥ ሂደት ላይ እንደነበረ ዴይሊይ ሜል የተባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ አጋልጧል። ይህ በለንደን ከተማ ከሚገኙ ምርጥ ከሚባሉ ቦታዎች አንዱ በሆነው አካባቢ የሚገኘው የኢትዮጵያዊ ኤምባሲ ቀደም ብሎ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ከእግሊዝ መንግስት እንደገዙት የሚታወቅ ሲሆን፣ የወያኔው አገዛዝ ይህን ህንጻ ለሽያጭ ያቀረበበት ዋጋም ወደ 40 ሚሊዮን ዶላር እንደሚጠጋ ጋዜጣው ዘግቧል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ይህን የኢትዮጵያዊያን ኤምባሲ ሽያጭ በመደለልና በማገናኘት የተሳተፈ አሊ ዲዛይ የተባለ ፖሊስ እንደሚገኝበት ተገልጿል። ይህ የእንግሊዝ ፖሊስ ኢምባሲውን ቢሸጠው ኖሮ ከወያኔ አገዛዝ ሁለት ሚሊዮን ፓውንድ ሊከፈለው ስምምነት እንዳደረገ የመረጃ ምንጫችን ገልጿል።

ቀደም ብሎ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ጊዚያትና በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት ከተለያዩ ሃገራት ህጋዊ ያልሆኑና የተደራጁ ማፊያዎች ጋር በጋራ መስራታቸዉ እንዲሁም ካንዳንድ ለጋሽ ሃገራትና የገንዘብ ርዳታ ከሚያደርጉ ሃገራት ጋር ከፍተኛ የሆነ የሙስና ውንጀል እንደሚፈጽሙ መገለጹ አይዘነጋም። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ከኦነግ አባላት ጋር ለመደራደር ያደረገው ሙከራ መክሸፉ ታወቀ

በመለስ ቁንጮነት እየተመራ ያለው የወያኔው አገዛዝ በተለይም በትጥቅ ትግል እንቅልፍ እየነሱት ያሉትን ተቃዋሚ ሃይላት በተለያዩ ጊዚያቶች አንድ አንዶቹን ድምጥማጣቸውን አጥፍቻቸዋለሁ፣ ሌሎቹን ደግሞ አምበርክኪያቸዋለሁ እያለ በውሸት ዶክመንተሪ ፊልም አጋዥነት ኢትዮጵያዊያንን ሌት ከቀን እያደነቆረ ቢሆንም፣ ከእነዚህ ሀይሎች ጋር የድርድር ልመና እያደረገ እንደሚገኝ ታወቀ።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ካዲስ አበባ እንደዘገበው ለበርካታ ዓመታት ትጥቅ ትግል ሲያካሂድ የነበረውን የኦሮሞ ነጻ አዉጪ ግንባር ተዋጊዎች በመደምሰስ ሙሉ በሙሉ ለአገዛዙ እጇ እንዲሰጡ አድርጊያቸዋለሁ፤ ባሁኑ ሰዓት ኦነግ የሚባል ሃይልና እንቅሴውም የለም ብሎ ቢናገርም፣ በዓለም ሉተራን ቤተክርስቲያን አማካኝነት ከኦነግ ሃይላት ጋር ለመደራደር ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ እንደነበረ ዘጋቢያችን ገልጿል። ወያኔ ከኦነግ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተቃዋሚ ሀይሎች ጋር ጭምር ለመነጋገር ፈቃደኛ ነኝ እያለ ቢገኝም፣ ተቃዋሚዎች ግን ለወያኔው ጥሪ ጆሮ እንዳልሰጡት ውስጥ አዋቂ ምንጮችን ወቢ አድርጎ ሪፖርተራችን ዘግቧል።

ዘገባዉን በሚመለከት አስተያየታቸውን ለዘጋቢያቹን የሰጡት ያደታ ጃንካ የተባሉ ባዲስ አበባ ከተማ የቀራኒዮ ክፍለከተማ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ብሄረሰብ ተወላጅ እንደተናገሩት በርግጥ ወያኔ በቁጥጥሩ ስር ባለው ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ፕሮግራሞቹ ለሚያሰማቸው ልፍለፋዎች ማንም ጆሮዉን የሚሰጥ የለም። “በሃይማኖት ተቋማት አማካኝነት ኦነግን ወደ ድርድር ለማምጣት ያደረገው ሙከራም የማያስገርማቸው መሆኑን ለዚህም ምክንያታቸው ወያኔ ያሰበዉን ነገር ለመፈጸም ምንም ይሉኝታ የሌለው ሰው ይታዘበኛል የማይል ነጬን ነገር ጥቁር ነው እመኑኝ የሚል ቡድን በመሆኑ ይህም የእርቅ ሂደት ካልተሳካለት ሌላ መንገድ ለመፈለግ የማይተኛ አውሬ ጎጠኛ በመሆኑ ነው ብለዋል። በማከልም ስለወያኔ የጋጠወጥነት ስራ መስማት የሰለቻቸው መሆኑን ገልጸው ባሁኑ ሰአት እኔም ሆንሁ ሌላው ኢትዮጵያዊ የወያኔን ውድቀትን መፈለጉንና ጆሮውም ለመስማት በንቃት እየተጠባበቀ ያለው የወያኔን ውድቀት በማፋጠን ላይ ባሉ ተግባራት እንደሆነ አስረድተዋል።

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## ብዙ የተወራለት ግልገል ጊቤ ቁጥር ሁለት በተመረቀ በሳምንቱ እንደተዘጋ ታወቀ

አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ለፖለቲካ ሲል ተጣድፎ የመረቀው የግልገል ጊቤ የሀይል ማመንጫ የተወሰነ ክልፍ መፍረሱን ግንባታውን ያከናወነው ሳሊኒ የተባለው ኩባንያ አስታወቀ።

የወያኔ አገዛዝ ፖለቲካው እንዳይበላሽበት በመፍራት የግንባታውን መፍረስ ከኢትዮጵያ ህዝብ በመደበቅ በሚስጥር ለመያዝ ቢሞክርም ታዋቂ የሆኑት መንግስታዊ ድርጅቶች ዜናውን ይፋ ካደረጉት በሁዋላ፣ ኩባንያው ለማመን ተገዶአል።

እጅግ የሚገርመው እዳውን ኢትዮጵያውያን እንደሚከፍሉት እየታወቀ ወያኔ ግን መረጃውን ከህዝብ ለመደበቅ ያደረገው ጥረት ነው የሚሉት የውሀ ምርምር ባለሙያ አቶ ሽፈራው ሲሳይ፣ አንዳንድ የአለማቀፍ ድርጅቶች እንደዘገቡት የችግሩ ምንጭ ሙስና ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ወያኔ ያለጫረታ ለጣሊያኑ ሳሊኒ ኩባንያ የሰጠው እርዳታው በአብዛኛው ከጣሊያን መንግስት የተሰጠ በመሆኑ እንዲሁም ከተሰጠው እርዳታ ውስጥ የወያኔ ከፍተኛ ሹማንቶች በጉቦ መልክ ዳርንጎት በመቀበላቸው መሆኑን አቶ ሽፈራው ተናግረዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆኑ የህወሀት ኩባንያዎችም በእቃ አቅርቦትና በተለያዩ መንገዶች ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከ ግንባታው ማጋበሳቸው የተጠቆመ ሲሆን፣ በዚህም የተነሳ ስራው በጥራት ጉድለት እንዲጠናቀቅ ሆናል ተብሎአል። የግንቦት7 ራዲዮ ከሁለት ሳምንት በፊት ከግልገል ጊቤ ምርቃት ማግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ተደጋጋሚ የሆነ መብራት መቋረጥ መከሰቱን መዘገቡ ይታወሳል።

## ወጣቶች ወያኔ ላወጣው የወታደር ቅጥር ማስታወቂያ አሉታዊ ምላሽ ሰጡ፣ ችግር ውስጥ የገባው ወያኔ ድጋሜ ምልመላ ለማድረግ መመሪያ አስተላለፈ

የመከላከያ ሰራዊትን ጥለው የሚጠፉ ወታደሮች ቁጥር ያስደነገጠው ወያኔ፣ ባለፈው ወር መግቢያ አዳዲስ ወታደሮችን ለመመልመል ያደረገው ሙከራ በወጣቱ እምቢተኝነት ከከሸፈ በሁዋላ፣ በብሄራዊ ተጠባበቂ ጦር ስም ምልመላ ለማድረግ በመላ አገሪቱ ትእዛዝ ያስተላለፈ መሆኑን ወታደራዊ ምንጮቻችን ገለጹ።

ሰሞኑን በደረሰን ወታደራዊ መረጃ መሰረት ወያኔ ብሄራዊ ተጠባበቂ ጦር በሚል ስም ወጣቱን ወደ ውትድርና ለማስገባት ስልት የቀየሰ ሲሆን፣ በዚህ ስልት መሰረትም በመላ አገሪቱ የሚገኙ ቀበሌዎች በነፍስ ወከፍ አስር ወጣቶችን ለውትድርና መልምለው በየወረዳው ለሚገኙ የሚኒሻና ጸጥታ ዘርፍ ጽ/ቤቶች ካስተላለፉ በሁዋላ ጽህፈት ቤቶችም የወጣቶችን ስም ዝርዝር እስከ ጥር 22 ቀን 2002 ዓም ድረስ ለመከላከያ ሚኒስቴር እንዲልኩ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸዋል።

የመከላከያ ሰራዊት አባላት ባለባቸው ብሶት የተነሳ በየጊዜው መከላከያን እየተው የተቃዋሚዎችን ጎራ በመቀላቀል ወይም በጎረቤት አገሮች ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ ሲሆኑ፣ በዚህ እርምጃ ከፉኛ የተደናገጠው ወያኔ ያለፈቃድና ያለበቂ ማስረጃ ወደተለያዩ ቦታዎች የሚሄዱ የሰራዊት አባላት ምርመራ እንዲካሄድባቸው ትእዛዝ ማስተላለፉ ታውቋል። የሰራዊቱ የኑሮ ሁኔታ እንደሌላው የህብረተሰብ ክፍል ሁሉ እጅግ አስከፊ መሆኑን የሚናገሩት ወታደራዊ ምንጮቻችን፣ ጥቂት የትግራይ ተወላጅ አመራሮች በተንፈላሰሰ ቪላ እየኖሩ አብዛኛው ወታደር ግን ልብሱንና ጫማውን መቀየር በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ መገኘቱ ለብሶቱ አንደኛው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የደደቢት የብድርና ቁጠባ ተቋም ሌላው የወያኔ የገንዘብ ማግበስበሻ ተቋም መሆኑ ተጋለጠ

በቅርብ ቀን የወጣ አንድ ጽሁፍ የደደቢት የብድርና ቁጠባ ተቋም በትግራይ ክልል የብድር አገልግሎትን ለመስጠት በሚል ሽፋን የተቋቋመ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መሆኑንና ተቋሙም ቀደም ብሎ እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1978 ተቋቁሞ ከነበረው የትግራይ ርዳታ ድርጂት መልኩን ቀየር አድርጎ የተወለደ መሆኑን ገልጿል። ተቋሙ ቀደም ብሎ ሲመሰረት ይዞት የተነሳው ዓላማ በትግራይ ክልል ለሚገኙ ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎች ኑሮ ማሻሻያ የብድር አገልግሎት መስጠት የሚል ይሁን እንጂ በተግባር ማንነቱ ሲታይ ግን ሌላው የወያኔ የረቀቀ የገንዘብ ማግበስበሻ የሽፋን ተቋም መሆኑን ጽሁፉ ገልጿል።

የደደቢት የብድርና የቁጠባ ተቋም ፈጣን የሆነ እድገትንና የስራ ስፋትን አሳይቷል በሚል ቀለም ቅብ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እውቅናን አግኝቶ የደደቢት የብድርና ቁጠባ ተቋም የሚል ስም ተሰጥቶት በሰፊው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጂት ሲሆን 25 በመቶ በመንግስት 75 በመቶ ደግሞ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የባለኔትነት ድርሻ ያለው እንደሆነ ጽሁፉ አብራርቷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ነፃ ተቋማት በሌሉበት የምርጫ ውጤት የሕዝብን ፍላጎት ገላጭ መሆን አይችልም፤ ለማይቀረው ሁለገብ ፍልሚያ ታጥቀን እንነሳ!!!

ሰሞኑን ወያኔ እርስ በርሱ የተጣላ ጽሁፍ ለአባላቱ በትኖ እንዲሸመድዱ እያደረገ ነው። የጽሁፉ ደራሲ መለስ ዜናዊ መሆኑ በያዛቸው ውሸቶች፣ በጨኸትና ፉከራው ብዛት መገመት ይቻላል። ወያኔ ችግር ውስጥ በገባበት ጊዜ ሁሉ እንዲህ ዓይነቱን አደናጋሪ ጽሁፍ መበተኑ የተለመደ ነው።

የጽሁፉ መነሻ ሃሳብ በሚቀጥለው ምርጫ ተቀዋሚዎች ብጥብጥ ያስነሳሉ የሚል ጭፍን መላምት ነው። አዕምሮ ያለው ሰው ጽፎት ቢሆን ኖሮ የብጥብጡን ምክንያቶች ለማወቅ በጣረና የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ባሳሰበ ነበር። የመለስ ጭንቅላት ግን ለዚህ አልታደለም። ለምን ተቃዋሚዎችም ሆኑ ሕዝብ ለብጥብጥ ሊነሳሱ ይችላሉ ተብሎ ተገመተ? ብሶት አላቸውን? ካላቸውስ በምን ምክንያት? የሚሉና የመሳሰሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች አያነሳም። የጽሁፉ ደራሲ በደፈናው ተቃዋሚዎችን በፀረ–ሰላም ኃይልነት በመፈረጅ ወያኔን የሰላምና የመረጋጋት አድባር አድርጎ ይሾማል። አገር በመበጥበጥ ተወልዶ፣ በመበጥበጥ አድጎና ገርጅፎ ዛሬ ክፍለ አህጉሩን እያመሰ ያለውን ወያኔ የሰላም አድባር፤ ሌሎቹን ደግሞ ጠበኛ አድርጎ ሲያቀርባቸው ትንሽ እንኳን አያፍርም። ይኸ እፍረተ–ቢስ ጽሁፍ "የ97ን ስህተት ላለመድገም" በሚል ተደጋጋሚ ሃረግ መሪነት መፍትሄ ብሎ ያቀረበውም ያው ወያኔ የሚታወቅበት አፈናን ነው። እርግጥ ነው በዚህ ሰነድ አማካይነት ለምርጫ 2002 ተስማሚ ነው ብሎ የተመረጠው የአፈና ዓይነት አስቀድሞ የታወቀው ቢሆንም በከፋቱና በጥልቀቱ ግን ለየት ይላል። ጽሁፉ እያንዳንዱ የወያኔ አባል ሰላይ በመሆን በተለይ የተቃዋሚ መሪዎችን እንቅስቃሴ በቅርብ እየተከታተለ ሪፖርት እንዲያደርግ በጥብቅ ያሳስባል። የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ በድምጽም በምስልም መቅረጽ በኋላ ለሚደረገው ነገር አጋዥ ይሆናል በማለት ከምርጫው በኋላ ሊደረግ የታሰበ ነገር መኖሩን ይጠቁማል። ሰነዱ የእርስ በርስ መሰላለልን እንደመልካም ነገር በዜጎች ሁሉ መተግበር አለበት ብሎ ይሰብካል። የተቃዋሚ ፓርቲዎች በሞላ አንዳች ቅን ነገር እንደማያስቡ፤ ቅን አሳቢነት ለወያኔ ብቻ የተሰጠ ቅብዓት እንደሆነ ለማሳመን ይሞክራል። በዚህም ምክንያት ከወያኔ በስተቀር አንድም የሚታመን ፓርቲ የሌለ በመሆኑ ሁሉንም በዓይነ ቁራኛ መከታተል እንደሚያስፈልግ ይወተውታል። ወያኔ ሰላማዊ መንገድ ያዋጣናል ብለው በምርጫ ሊወዳደሩት የተዘጋጁትንም ሳይቀር ከሕዝብ ለመነጠል ያለመ መሆኑን ሰነዱ ይጠቁማል። የዚህ ሰነድ ዋነኛው መልዕክት ወያኔ አቅም ካገኘ ለማንም የማይመለስ መሆኑን ነው።

በዚህ ሰነድ የተጠመቁት የወያኔ አባላት በተራቸው ወጣቶችን፣ ተማሪዎችን፣ የቀበሌ ነዋሪዎችን፣ ሠራተኞችን እና በገጠር ደግሞ አርሶ አደሮችን እያባበሉም እያስገደዱም በመሰብሰብ መነዝነዝ ጀምረዋል። በዚህም ምክንያት የዘንድሮ ምርጫ በእጩዎች ክርክር ፋንታ የካድሬዎች ንዝነዛ የበዛበት ሆኗል።

ለመሆኑ ከዚህ የወያኔ ጽሁፍ ምን እንማራለን? ምንም። ከጽሁፉ የምንማረው አንዳችም አዲስ ነገር የለም። ሆኖም ግን ይህ ጽሁፍ ቀድሞ የነበሩንን እምነቶች በማስረጃነት የሚያጠነክርልን በመሆኑ ጠቃሚ ሆኖ አግኝተነዋል።

1. ይህ ጽሁፍ ወያኔ በምንም ዓይነት በምርጫ ሊወገድ እንደማይችል ያረጋግጣል። እንዲያውም ከዚህ ምርጫ በኋላ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መኖር ፈጽሞ እንደማይፈልግ ይጠቁማል፤
2. የዚህን ምርጫ ተብዬ ድራማ ውጤት አስቀድሞ ካቀደው በትንሹ እንኳን እንዲዛነፍ የማይፈልግ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ሰነዱ በዚህ ምርጫ አንዳችም ያልተጠበቀ ውጤት መምጣት እንደሌለበት በማያሻማ መንገድ ግልጽ አድርጓል፤
3. አንዳንድ ፓርቲዎች ከወያኔ ጋር ለወራት ተደራድረን ፈረምን በማለት እንደስኬት የሚያወሩለትና በኋላም ህግ ሆኖ የወጣው "የሥነ–ምግባር ደንብ" ሌሎች ፓርቲዎችን እንጂ ወያኔን እንደማይገድብ በተግባር አረጋገጧል። ይህ ጽሁፍ የወያኔ አባላት በተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ላይ እንዲወስዱት የሚገፋፋቸው እርምጃዎች ሁሉ በሥነ–ምግባር ህጉ መሠረት ህገወጥ ናቸው። ወያኔ ግን በየመሥሪያ ቤቱና ቀበሌ አዳራሾች በድምፅ ማጉያ ይናገራቸዋል።
4. በመጨረሻም፤ ሰነዱን በጥንቃቄ ያጠና ሰው ወያኔ ላይ ላዩን የተረጋጋ ይመስል እንጂ ክፉኛ መረበሹን እና ከምርጫው ውጭ የፈራው ነገር እንዳለ ይገነዘባል።

ወያኔ ለስልጣን ባለው ስስት እና እየመጣበት ባለው አደጋ ፍርሃት መካከል ተንጠልጥሏል። በአንድ በኩል ምርጫ የመሰለ ነገርን ተውኖ ተመረጥኩ ማለትና በሥልጣን መደላደልን ይፈልጋል፤ ሆኖም የምርጫ ወሬ ምርጫ 97ን እያስታወሰ ያስበረግገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከምርጫው በፊት ይሁን በኋላ ያልታወቀ፤ ሊከላከለው የማይችል አደጋ እየመጣበት እንደሆነ ታውቆታል። ይህ ምርጫ ከዚያ አደጋ እንደማይታደገው ያውቃል። እናም ወያኔ ተምታቶበታል።

ሕዝባችን ለዘንድሮው ምርጫ ደንታ የሌለው መሆኑ የታወቀ ነው። ከምርጫው በኋላ ተመርጠዋል ተብሎ የሚነገረው የወያኔ እጩዎችና ጥቂት አድርባዮች እንደሚሆኑ ያውቃል። አድርባዮችም ቢሆኑ ስማቸውን ማስመዝገብ እንጂ የምር መፎካከር አያስፈልጋቸውም። እንዲመረጡ በተወሰነበት ቦታ ባይመረጡም ይመረጣሉ፤ በማይፈለጉበት ቦታ ደግሞ ቢመረጡም አይመረጡም። የምርጫው ውጤት ከቢሮ እንጂ ከምርጫ ሳጥን አይወጣም። እነሱም ይህንን ያውቃሉ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ወያኔ ይፈራል። ምንድነው የወያኔ ፍርሃት ምንጭ? ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህ ምርጫ የሚጠብቀው ነገር የለም። በዚህ ዓመት የሚደረገውን የይስሙላ ምርጫ በተመለከተ ሕዝባችንም የሚከተሉትን እርምጃዎችን በተራ እንዲወስድ ጥሪ ያደርጋል:–

1. አሁን በጀመረው መንገድ ለወያኔ ለምርጫ ተመዝገቡ ጥሪ ጆሮውን አለመስጠት ፈጽሞም ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ዝር አለማለት፤
2. በስህተት የተመዘገበ ቢኖር ለመራጭነት ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አለመሄድ እና ግንቦት 7 በጊዜው የሚያቀርበውን ጥሪ በንቃት መጠባበቅ፤ እና
3. ድምፅ መስጠት ግዴታ ከሆነበት ደግሞ ወረቀቱን በማበላሸት ተቃውሞን መግለፅ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል።

በተጨማሪም

- በሰላማዊ መንገድ ለውጥ እናመጣለን ብለው ከልባቸው አምነው ውድድር ውስጥ የገቡ ፓርቲዎች ካሉ የሚፋለሙት ከቆሰለ አውሬ ጋር መሆኑን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በትህትና ይመክራል።
- ምርጫውን በሚመለከት ከግንቦት 7 ጋር ተቀራራቢ እምነት ያላቸው ድርጅቶች ሁሉ ለደጋፊዎቻቸውም ሆነ ለሕዝባችን ተመሳሳይ መልዕክት እንዲያስተላልፉ ጥሪውን ያቀርባል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ነፃ ተቋማት የሌሉበት፤ ወያኔ ራሱ የሚያስተዳድረው ምርጫ የሕዝብ ፍላጎት መግለጫ፤ ውጤቱ ደግሞ የሕዝብን ፍላጎት ገላጭ ሊሆን ፈጽሞ የማይችል በመሆኑ ለማይቀረው ሁለገብ ፍልሚያ ታጥቀን እንነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

### ወጣቶች ወያኔ ላወጣው የወታደር ቅጥር . . . ከገጽ 1 የዞረ

ምክንያት መሆኑን ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰራዊቱ ምንም እርባና በሌለው የሶማሊያ ጦርነት ውስጥ ገብቶ እንዲያልቅ መደረጉ፣ በባድመ ጦርነት ያለቀው ከሰባ ሺ በላይ ወጣት ሳያንስ ባለቀ ና በሞተ ጉዳይ ላይ እንደገና ከኤርትራ ጋር ጦርነት ለመግጠም መዘጋጀቱ፣ በመከላከያ ውስጥ ያለው የትግራይ ተወላጆች ፍጹም የበላይነትና በሌሎች ብሄሮች ተወላጆች ላይ የሚደርሰው እንግልት ሰራዊቱ መከላከያን እየተወ ተቃዋሚዎችን እንዲቀላቀል ምክንያት ሆኖታል ተብሎአል።

እስካሁን ድረስ ባለው መረጃ በተለይ ከግንቦት97 ምርጫ በሁዋላ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት መጥፋታቸው የታወቀ ሲሆን፣ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ሊጠፉ የተዘጋጁ የሰራዊት አባላት ቁጥርም በዚያው ልክ መሆኑን ወታደራዊ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል። አብዛኛው ሰራዊት አማራጭ በማጣትና ቤተሰቡን ለመርዳት ሲል መከላከያን ቢቀላቀልም፣ አሁን ባለው የኢኮኖሚ ቀውስ ቤተሰቡን ለመርዳት ቀርቶ እራሱንም ማኖር ባለመቻሉ "አማራጭ አጥቼ ነው የገባሁት" የሚለውን ምክንያት እየተወ ስደቱንተያይዞታል። በርካታ ወታደሮች ወደ ጎረቤት አገሮች ከተሰደዱ በሁዋላ አንድም ተቃዋሚዎችን እንደሚቀላቀሉ ሌላም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን አማካኝነት ወደ አውሮፓና አሜሪካ እንደሚጓዙ ታውቋል።

ወያኔ የሚጠፉት ወታደሮች ተቃዋሚዎችን በመቀላቀል መልሰው ይወጉኛል ብሎ በመጨነቅ ላይ ሲሆን፣ ይህንን ሁኔታ ለማስቀረትም የተለመደውን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ደረቅ ፖለቲካ በየጊዜው ሰራዊቱን እየሰበሰበ በማጠጣት ላይ ይገኛል። አንዳንድ የመከላከያ ሰራዊት አባላት "ኢኮኖሚያችን አደገ ሲባል እንሰማለን፣ → የህዝቡ ኑሮ ግን ቁልቁል ሲምዘገዘግ ነው የምንመለከተው፣ ሰላም አለ ይባላል እኛ ግን የምናውቀው ለውጊያ ተዘጋጁ ተብሎ ነው ሲነገረን ነው፣ በምግብ ራሳችንን ችለናል ይባላል በርካታ ህዝብ ግን አይናችን እያየ ሲያልቅ እየተመለከትን ነው፣ የብሄረሰቦች እኩልነት አለ ይባላል በተግባር የምንመለከተው ግን የአንድ ብሄር የበላይነት ነው፣ ዲሞክራሲ አለ ይባላል ዜጎች ግን ሰላማዊ ሰልፎችን ማድረግ ተከልክለዋል፣ የፕሬስ ነጻነት አለ ይባላል፣ በርካታ ጋዜጠኞች ግን ሲታሰሩና ሲሰደዱ እየተመለከትን ነው" የሚሉ ጥአቄዎችን እንደሚያነሱ ምንጮቻችን ገልጸው፣ እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎችን የሚያነሱ ደፋር ወታደሮች በማግስቱ የሚደርሱበት እንደማይታወቅ አክለው ተናግረዋል። የአብዛኛው ወታደር ጥያቄ ተመሳሳይ በሆንም፣ ወታደሩ ጥያቄውን አንግቦ በአንድነት እንዳይነሳ ጥቂት የህወሀት ሰላዮች በማጨናገፍ ላይ በመሆናቸው ወታደሩ የሆዱን በሆዱ እያደረገ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መጥፋትን እንዳማራጭ እየተጠቀመበት ነው።

የግንቦት7 አመራሮች የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለሰራዊቱ በተደጋጋሚ ባስተላለፉት መልእክት፣ ሰራዊቱ በላበት ሆኖ በስውር በመደራጀት አገዛዙን እንዲያዳክም መናገራቸው ይታወሳል። የአማራ ተወላጅ የሰራዊት አባላት የሚአሰሙት ተቃውሞ እየጠነከረ በመምጣቱ ወያኔ የተወሰኑ የአማራ የጦር መኮንኖችን በመፈንቅለ መንግሰት ሙከራ ስም ለማሰር ቢችልም፣ እንቅስቃሴውና ተቃውሞው ግን እየበረታ ከመሄድ ውጭ ሊበርድ እንዳልቻለ ወታደራዊ ምንጮቻችን ይናገራሉ። በርካታ የአማራ ተወላጅ የሰራዊት አባላት በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞ ላይ በተወሰደው የሀሰት እርምጃ በእጅጉ መበሳጨታቸውን ለማወቅ ተችሎአል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 91 የካቲት 4 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# የሕዝብ ኑሮ፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በኢትዮጵያ መሬት ላይ (ክፍል 4 ካለፈው የቀጠለ ከፍስሐ ዘማርያም)

ኢሕአዴግ መንግሥት ከሆነበት ቀን አንስቶ ፍጹም ትኩረት ከነፈጋቸው የትምህርት ጉዳዮች መሀል አንደኛው ይኸው መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (Non Formal Education) ነው:: (ምናልባት ደርግን ስለሚጠላ ይሆን ይህን ያደረገው?) ሁለት ዓሠርት በሚጠጋው የሥልጣን ዘመኑ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አገልግሎት ረገድ የተፈጠረውን ሰፊ ጉድለት ማጤን የጀመረው ገና ከሦስትና አራት ዓመት ወዲህ ነው:: ያውም በእርዳ፤ ሰጪዎች ግፊት! እንደዚያም ሆኖ እስካሁን የተጨበጠ ለውጥ አል፤የም:: መሐይምነትን በመዋጋት ረገድ የታየውን ፍጹም እንዝህላልነት የሚገልጸው ከሆነ፤ አንድ የሚያሳፍር ገጠመኝ ላካፍላችሁ:: ነገሩ የሆነው ከአንድ ሁለት ዓመት በፊት ነው:: ትልቅ አውደ ጥናትና የምክክር መድረክ ከአዲስ አበባ ውጭ በአንድ ትንሽ ከተማ ተዘጋጅቷል:: ዓላማው በሐገር አቀፍ ደረጃ እንዲጀመር ለታቀደው መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት) መርሐ ግብር ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ነው:: በስብሰባው ላይ የትምህርት ምክትል ሚኒስትሩ የሁሉም ክልሎች ትምህርት ቢሮ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ሃላፊዎችና የትምህርት ባለሙያዎች ተገኝተዋል:: የጥናት ጽሁፍ ካቀረቡት መካከል አንድ ኡጋንዳዊ የጎልማሦች ትምህርት ባለሙያ ይገኛል:: ኡጋንዳዊው ንግግሩን የደመደመው ተስብሳቢውን ሁሉ ባሸማቀቀና አንገት ባስደፋ የእጅ አዙር ወቀሳ ነው:: ቃል በቃል ባይሆንም:

*በኡጋንዳ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (መሠረተ ትምህርት) መርሐ ግብር "ሀ" ብለን የጀመርነው ከሠላሳ ዓመት በፊት ነው:: ያኔ ምንም ልምድ አልነበረንም:: ኡጋንዳን መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (Non Formal Education) ያስተማራት አውሮፓዊ ወይም አሜሪካዊ አይደለም:: ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ነው!! ያ ሰው ዛሬ እዚህ ከፊት ለፊት ቀምጧል (ባለሙያውን ስሙን ጠርቶ እያመለከተ):: ኔን የቀድሞ ተማሪውን ገለጻ እያዳመጠ ማስታወሻ ሲወስድ እየተመለከትኩት ነበር:: እኔ እሱን (ልብ አድርጉ! ኢትዮጵያን እንደ ማለት ነው) ልናሳስተምርን አልተመቸኝም:: ይህን እናንተ እንዴት እንደምትመለከቱት አላውቅም:: ለኔ ግን እያስጨነቀኝ ነበር:: ግራ የሚያጋባ ነገር ነው የሆነብኝ:: አስቡበት:: አለ በትህትና::*

## የኢኮኖሚ ለውጡና ድህነትን ማስወገድ

እንግዲህ ረሀብና እርዛቱ፤ መጠለያ አልባነቱ፤ መሐይምነቱ ወዘተ የህጻናት፤ የወጣቶች፤ የጎልማሦችና የአረጋውያን፤ የወንዶችና የሴቶች በአጠቃላይ የዜጎች የአዘቦት ሰቆቃ በሆነበት ሐገር ነው ያለነው:: ይህ አስከፊ ትእይንት የሚታየው፤ የዜጎቹን መሠረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች እንዲያሟላ የሚጠበቅበት መንግሥት የሚባል ተቋም ባለበት ሐገር ነው:: የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶችን በሕገመንግሥቱ ወረቀት ላይ አስፍሮና ተዛማጅ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችንም ተቀብያለሁ ስለሆነም ለማሟላት የታቀደ ጥረት አደርጋለሁ ብሎ ቃልየገባ መንግሥት ባለበት ሐገር ነው:: ይህ ብቻም አይደለም:: በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት (የማን መንግሥት ነው?)፤ የበለጸጉ ሐገሮችን ሳይቀር የሚያስንቅና የሚያስቀና ባለ ሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት ለተከታታይ ዓመታት አስመዝግቤያለሁ እያለ ጉራ ሲነዛና ያለህፍረት ጮቤ ሲረግጥም የምንታዘብበት ሐገር ነው::

በዚህ ሐገር በእርግጥ የኢኮኖሚ ለውጥ አለ:: መንገዶች፤ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ተገንብተዋል:: ቁጥራቸው የበዛ ህጻናትና ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ችለዋል:: የትምህርቱ ጥራት ጉዳይ ሳይነሳ:: ኢሕአዴግ በትምህርት ዘርፍ ፊቱን ወደ ጥራት ጉዳዮች ለመመለስ የምር ጥረቶች ሲያደርግ አይታይም:: አሁን የተያዘው የትምህርት ጥራት ፓኬጁ ዲስኩርና ፋይዳው ከምርጫ 2002 ይዘል እንደሆነ የሚታይ ነው:: የአበባና የፎቁ ልማት ለብዙ ሰው የሥራ ዕድል መፍጠሩም ይ፤ያል:: ሰቆቃችንን እየደበቀብን ተቸገርንና ነው እንጂ፤ ፎቁ የሌሎችም ቢሆን እኛም ለዓይናችን ደስ ይለናል:: ፎቁም ሆነ አበባው ባለቤቱን ከመጥቀሙም ባሻገር ለመንግሥት የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ የግብርና የቀረጥ ትርፍ ግን ይበልጣል:: በመሠረቱ የመንግሥት ትርፍ ማለት የሕዝብ ትርፍ ማለት አይደለም:: የመንግሥት ገቢ መጨመር የሕዝብ ትርፍ የሚሆነው የሕዝብ መንግሥት ባለበት ሐገር ነው:: ሁሉም የኢሕዴግ ለውጥ ተደምሮና ተቀንሦ የምናገ-ው የመጨረሻ አጠቃላይ ውጤት ግን ድህነት አለመወገዱን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ 3ዲያውም ለከፋ የኑሮ ውድነት ተዳርጏል:: እኛን፤ ትናንትናም ሆነ ዛሬ እጅግ እየበላን ያለውና በቅድሚያ እንዲታከክልንና እፎይ፤ እንድናገኝ የምን በት ዋናውና አጣዳፊው ችግራችን ያለው ሌላጋ እንጂ የአበባና የፎቅ ለውጦቹ ጋ አይደለም:: በአጠቃላይ ሕዝብን ከድህነት ያላላቀቀ ለውጥ የነሱ እንጂ የኛ ለውጥ ሊሆን አይችልም:: የበላንን የሚያክልን መንግሥትና ፖሊሲ ነው ፍላጎታችን:: ፍጹም ድህው ሆነ ዝቅተኛና መካከለኛ ኑሮ የሚኖረው በብዙ 10 ሚሊዮኖች የሚቆጠረው ሕዝብ የብልጭልጩ የኢኮኖሚ ለውጥ ጠቃሚ አይደለም:: የጥቂት በዪዎች ተመልካች ነው የሆነው::

የኢሕአዴግ መንግሥት የሚመጻደቅበት የድህነት ማስወገጃ ፖሊሲው የሚሊኒየም ልማት ግብና ስትራቴጂው በወረቀት ላይ የቀረ ከንቱ ህልም ሆኗል:: በተግባር ታየ የሚባለው የኢኮኖሚ ለውጥ (ባለ ሁለት አሀዝ ዕድገት) ሕዝቡን አሁን ከሚገኝበት አስከፊና አዋራጅ የድህነት ኑሮው ሊያላቅቀው ያልቻለ ለውጥ ነው:: የምግብ ዋስትናን እን ለማረጋገጥ ያልቻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ምን ዓይነትና የማን ዕድገት ነው? ሰብዓዊ ይዘትና ገጽ የሌለው የዜጎችን ኑሮ ያልለወጠና ያላሻሻለ ለውጥ ምን ዓይነትና የማን ለውጥ ነው? ናየድህነት ማስወገጃን ፖሊሲ፤ ግብ፤ ዒላማ፤ ስትራቴጂ የሚባለው ድሀውን ከረሣና የማያይ ከሆነ፤ ሌሎችን ደግሞ የባሰ ድሀ የሚያደርግ ከሆነ ምኑ ላይ ነው ናየድህነት ማስወገጃን ምናምን የሚባለው? ከ19 ዓመታት የኢሕአዴግ መንግሥትነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን አተረፈ? የገቢና ወጪው ሂሳብ ሲወራረድ የሚታየው ዋናው ሥዕል የሕዝብ ኪሣራና ኪሣራ ነው:: በአጭሩ በ19 ዓመት የግዛት ዘመኑ እንደፎከረው ዜጎቹን በቀን ሦስ መመገብ ይቅርና ለባሰ ድህነትና ረሀብ የዳረገ መንግሥት ምን ዓይነትና የማ መንግሥት ይሉታል? የኢኮኖሚ ብሶትና ተቃውሞውን ሊያሰማ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ለብቻው ሰልፍ ያደረገው ደፋሩ ኢትዮጵያዊ ወጣትም በራሱ መንገድ ያለው ይህንኑ ነው:: እኔ በረሀብ አለንጋ እየተገረፍኩ ባለሁበት ሁኔታ 'ጮእእክህ' ብላችሁ የምትናገሩለት የፎቅ፤ የመንገድ፤ የመብራት፤ የአበባ የለውጥ ዜና 'አይይይሰማአአም'፤ ሊታየኝ አልቻለም አይችልምም ነው ያለው:: አንድ ነገር ታደርጉ እንደሆነ አድርጉ ነው ያለው::

እኛ እያየን ያለነው ግን የእኛና የእነርሱ ኑሮ የሰማይና ምድር ያህል እየተራራቀ መሄዱን ነው:: ድህነት ለሚለው ቃል (ፅንሰሀሳብ) ዓለምም፤ ባለሙያዎቹም፤ እኛም ተራዎቹ ሰዎች ከምናውቀው የተለየ ትርጉም ሰጥተውት ይሆን እንዴ? ድህነት ማስወገድ ማለት የሥርዓቱና የባለሥልጣናት ወዳጅ፤ ዘመድና የጎጥ ልጅ የሆኑ የአየር ባየር ነጋዴዎችን ባንድ ጀንበር ሚሊዮኔር ማድረግ ነው? ሚሊዮኔር የነበሩ መሰሎቻቸውን በሙስና ባለብዙ ሚሊዮኔርና ቢሊዮኔር ማድረግ ይሆን? አለበለዚያ ለሕዝብ ጥቅምና ለልማት ዓላማ ስለመዋሉ አፋችንን ሞልተን የማንመሰክርለትን ግብር፤ ቀረጥና የውጭ ምንዛሪ ለመንግሥት የሚያስገኙ አዲስ የሐገር ውስጥና የውጭ ባለሐብቶችን መፍጠርና መንግሥታዊ ትርፍ ማጋበስ ድህነት ማስወገድ ሊሆን አይችልም:: በፌዴራልም በክልልም ያሉ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናትን በየትልልቅ የፋይናንስና የንግድ ኩባንያዎች ውስጥ በቦርድ አባልነትም በዋና የንግድ ሽሪክነትም እያየን ነው:: ከፓርቲ ንግድ ደርጅቶች ውጭም ማለት ነው:: ይህ ይሆን እንዴ ድህነት ማስወገድ የሚባለው? አንዳንዶቹ ባለሥልጣኖች በሕገ ወጥ መንገድ አፍርተው የሚደብቁት ሐብት በቻይና ከተሞች በሚንደላቀቁ ልጆቻቸው በኩል ተበትኖ - ተበትኖም የሚያልቅ አይደለም። እንዲያውም የልጆቹ መጥፊያ ሳይሆን ይቀራል?

## "መልካም ገጽታን ማበላሸት"

ይህ ዘግናኝና መራር ሐቅ ሲገለጽ በኢኮኖሚው "ባለድሎች" ዘንድ ከጭፍን ጥላቻና ቅናት በመነጨ መልካም ገጽታቸውን ለማበለሸት ወይም የፖለቲ ትርፍን ለማግኘት ሲባል የቀረበ አሉባል አድርገው ያቀርቡታል:: ዕውነትን ምክርና ጥቆማን ማየትና መስማት የማይፈልግ ሥርዓት ምላሹ ሁልጊዘ ይኸው ነው:: ለሌላው የሩቅ ተመልታች ደግሞ (ሐገር ውስጥም ሆኖ ሩቅ የሆነ ስንት አለ!) ይህ ሊሆን የማይችል ተራ ማጋነን እና ወሬ ማዳመቂያ መስሎ ይታየው ይሆናል:: የምር በማስተዋልና በማሰላሰል ዋናውንና ትልቁን ሥዕል ለማየት የማይሞክሩ ሌሎች ደግሞ ታዲያ አሁን ምን አዲስ ነገር መጣ? ድህነት ቀድሞም የነበረ አይደል እንዴ ይላሉ:: ሁሉም የራሳቸው ጉዳይ!! በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ወገኖች ሩቅ በሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድንኳን ውስጥ ስለሚኖሩ የጠኔውን ሐቅና የሕዝቡን ውርደትና መሸማቀቅ ለማየት ይችላሉ፤ ይፈልጋሉ ወይም ይጥራሉ ተብሎ አይጠበቅም። ሐቁ ግን ክፍት አእምሮና ስስ ስሜት ባለው ተመልካች ሁሉ ቁልጭ ብሎ ሊታይ የሚችል ነው። ይህ እኮ በደስታና በእርካታ የሚገልጹት መልካም ዜና አይደለም! በቃላት እየተራቀቁ የሚጽፉት የችለሮታ ማሳያ ድርሰትም አይደለም። በህሊና አስገዳጅነትና ለመፍትሔ መሻት ካልሆነ በስተቀር የራስን መዋረድ የሚያውጁበትን ይህን መሰሉን ሐቅ መግለጽ አይመችም። ኩራትን የሚፈታተንና ስሜትን የሚተናነቅ ልብ ሰባሪ ነገር መሆኑን የሚያውቅ ያውቀዋል።

## ግን ሕዝቡ ኑሮውን እንዴት ቻለው?

ብዙ ሰዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንዴት ነው ይህንን ኑሮ ችሎ እየኖረ ያለው? ብለው እንደየሁኔታው በማዘንም ግራ በመጋባትም ስሜት ውስጥ ሆነው ይጠይቃሉ:: ሕዝቡ በአስማት ነው የሚኖረው ወይስእንዴት ነው ብለው የሚገረሙም ጥቂት አይደሉም::

*አባዬ ትምህርት ቤት የሚቀርብ የአስማት ትርዒት ስላለ ለመግቢያ ሁለት ብር ብቻ ስጠኝ ሌላ አላስቸግርህም፤ ብሎ ተማሪ ልጅ አባቱን ይለምናል። አባት መለሰ የተባለውን ያልሰማ ይኖር ይሆን? ልጄ ደግሞ አስማተኛ ለማየት ሩቅ መሄድና ገንዘብ መክፈል ምን ያስፈልጋል። እኔ አስማተኛ አባትህ እዚሁ አለሁልህ አይደል ኢታየኝም እንዴ በምን አይነት አስማት መላ ቤተሰቡን በ400 ብር ደሞዝ ከወር እስከ ወር እያኖርኩ እንዳለሁ።*

ይህ እዚህ የቀረበው ለፈገግ አይደለም። ሚስጥሩ አልታይ አልፈ ሲል እውነትም አስማት ይሆን እንዴ ያስብላል ለማለት ነው። ሚስጥሩ ግን በከፊል ቀደም ብሎ በጤፉ፤ በበርበሬውና በከሰሉ ጉዳይ ላይ እንደተገለጸው ነው። በከፊል ደግሞ ወዲህ ነው። ይህ ኢትዮጵያ ነው! የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥልቅና ጥብቅ የቼይማኖት ታሪክና ባህል ያለው ሕዝብ ነው። አብዛ ውን ጊዜ የሆዱን ብሶትና በደሉን የሚያ ፍለው፤ አቤት የሚለውና ለቅሶውን የሚያሰማው ለፈጣሪው በግልና እዚያው በደጁ ተገኝቶ ነው - ተመስገን የባሰ አታምጣብኝ ማለትን ሳይዘነጋ። እና የኑሮውና የአኗኗሩ ሚስጥር በሩቅና በግዴለሽ ተመልካች ባይታይለት ለምን ይገርማል?

## ለሕዝቡ ብሶት የሚቀርብለት መንግሥታዊ ምላሽ - "አዲስ" የቅጣትና ሽልማት ሥርዓት

የኢትዮጵያ ሕዝብ የስቃይ ኑሮ ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ ብሶበታል። በምርጫ 97 ድበጹ ተዘርፏል።ባልመረጠው መንግሥት ለመገዛት ተፈርዶበታል። የዚህ ቀጥተኛ ውጤት የሆነው የኑሮ ውድነቱ ብቻ ሣይሆን ዝርፊያው፤ የፖለቲካ ጭቆናና አፈናው፤ የሁሉም ዓይነት መብት ረገጣው፤ የዘር መድልዎውና የጎሣ ግጭቱ፤ ከሥራና መኖሪያ ማፈናቀሉና ሐገር ቆርሶ መሸጡ ሁሉም ከቀድሞው ብሷል::

በዚህ ሐገር፤ ዓለም የሚያውቀውና የሚሠራበት የሽልማትና የቅጣት ዓላማና ሥርዐቱ ሁሉ ተገለባብጧል። ሊመሰገን ሊሾም - ሊሸለም የሚገባው ይወገዛል፤ ይገለላል፤ ይቀጣል። ሊገሰጽ፤ ሊታረም ልሆነም ሊቀጣ የሚገባው ሰነፉ፤ አውደልዳዩ፤ ሠላዩና ህሊናውን የሸጠው አድርባይ ደግሞ ልዩ ጥቅም ይሰጠዋል፤ ይሾማል፤ ይሸለማል:: ዋናው ነገር የደሞዝ ጥቅምና የደረጃ እድገት ብቻ የሚያስገኝ የትምህርት ማስረጃ ከየትም እንደምንም ብሎ ማቅረብና የታማኝነት ማረጋገጫ የሆነውን የኢሕአዴግ ፓርቲ ደብተር ይዞ መገኘት ነው። በእምነትም በተግባርም እንደሚታየው በዚህ ሥርዓት ቅድሚያ የሚሰጠው ለሙያ ግዴታና ለሥራ ሃላፊነት ብቁ የሚያደርግ (በአንጻራዊነት) ጠንካራ ሥልጠና ለወሰደ፤ የተረጋገጠ የሥራ ብቃት፤ ቁርጠኝነትና ልምድ ይዞ ለተገኘ ባለሙያ/ሠራተኛ አይደለም። በፍጹም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ሠራተኛ የኢሕአዴግ አባልነት ፎርም ስላልሞላ ብቻ በሰበብ አስባቡ ተገፍቶ ከአገልግሎት ውጭ እየተደረገ ነው:: በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ሰፍኖ የሚታየው በፖለቲካና በዘር መድልኦ ላይ የተመሠረተ የሽልማትና ቅጣት ሥርዓት ነው። ይህንን አድሏዊ ሥርዓት ለመሸፋፈን እያገለገለ ያለው ደግሞ ከአነዳደፉ ጀምሮ እስከ አፈጻጸሙ ድረስ ሆን ተብሎ እንዲዛባ የተደረገው ናየሥራ ሂደት ማሻሻያን - ቢፒአር የተባለው መርሐ ግብር ነው። በዚህና በመሳሰለው ሰበብ ከሥራ የተንሳፈፈው ከደረጃው ዝቅ የተደረገው ወይም የተፈናቀለው ዜጋ ቀጥሩ እጅግ ብዙ ነው።

ይህንን ተከትሎ የስንቱ ቤተሰብ ለባሰ ረሀብና ለጎዳና ተዳረገ? በዚህ የተነሳ ቤተሰባቸውን መመገብ ተስኗቸው በሀሳብና በሰቀቀን ብዛት እንደ እብደት ያደረጋቸው፤ መንገድ ላይ ለብቻቸው የሚያወሩና የሚሰሩትንሳያውቁ ለተለያየ አደጋ የሚጋለጡትን ቤቱ ይቁጠራቸው። በጣም የሚያሳቅቀው ደግሞ ችግራቸውን በቅጡ ልተረዱ ልጆቻቸው ለሚቀርብላቸው ይህንን-ያንን አምጣ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት መቂስ መጥፋቱ ነው:: ዓይኑ እያየ ቤተሰቡ በረሀብ አለንጋ ከሚገረፍ ብሎ፤ ሁኔታውን ለመቀየርም ምንም አቅም ወይም ተስፋ ሲያጣ ቤተሰቡን ከቤት ትቶ የሚጠፋና የት እንደደረሰ እንኳ ሳይታወቅ የሚቀር ስንቱ ነው? ከዚህም በባሰ ይህ ጸሐፊ እንኳ ከአንድ ሁለት ወረዳ ብቻ በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ያጠፉ የስድስት ሰዎችን አሳዛኝ ታሪክ (ከአንድ ራሱም በዚህ ስሜትና አዝማሚያ ውስጥ ከሚገኝ ሰለባ) ሰምቷል።

(ክፍል 5 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል)

## በአዲስ አበባ የሚመዘገቡ መራጮች በመጥፋታቸው ወያኔ የቤት ለቤት ቅስቀሳ ጀመረ

አዲስ አበባ ህዝብ ለመጪው ምርጫ የሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ በተደጋጋሚ ከተገለጸ በሁዋላ፣ ወያኔ ካድሬዎችን በነዋሪዎች ቤቶች በመላክ እንዲመዘገቡ እየቀሰቀሰና እያስፈራራ መሆኑ ታወቀ።

ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ እንደዘገበው ወያኔ በተመዝጋቢ መራጮች መጥፋት ክፉኛ በመደናገጡ፣ ካድሬዎችን በየሰዎች ቤቶች ከመላክ አንስቶ በድምጽ ማጉያ መሳሪያዎች በመጠቀም በእየመንገዱ ቅስቀሳ እያደረገ ነው። ይሁን እንጅ ይላል ሪፖርተራችን ህዝቡ ለወያኔ ጥሪ ምንም አይነት አወንታዊ ምላስ ሊሰጠው አልቻለም። ወያኔ ሰሞኑን የምርጫውን ቀን ማራዘሙም ይታወቃል።

ግንቦት7 ውጤቱ አስቀድሞ በታወቀ የይስሙላ ምርጫ ህዝቡ ተሳትፎ እንዳያደርግ ተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ህብረተሰቡም ለዚህ ጥሪ አወንታዊ መልስ በመስጠት ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን ገልጿል። በሁሉም መስክ የዘንድሮው ምርጫ በምርጫነት እንኳን ሊመዘገብ አይችልም የሚለው ዘጋቢአችን፣ መለስ ዜናዊ አውቆ የፈራ በመምሰል ህዝቡ እንዲመዘገብ የሚያደርገው ማታለልም እልዳልሰራለት ታውቋል። መለስ ዜናዊ የአርሶ አደሮች ቀን ብሎ በሚጠራው በአል ላይ ለተገኙ 500 ካድሬ አርሶ አደሮች ሽልማት ሲሰጥ ዋናው ንግግሩ ምርጫ ላይ እንደነበር ሪፖርተራችን አክሎ ገልጿል። ወያኔ ምርጫውን ለማሸነፍ አስፈላጊውን ስራ ሁሉ የሰራ በመሆኑ ሊፈራ የሚችልበት ነገር የለውም ያለው ዘጋቢያችን፣ ይሁን እንጅ የወያኔ ሰዎች በምርጫው ጭንቀት ውስጥ ያልገቡ ለማስመሰል የማያደርጉት ጥረት የለም ብሎአል።

በሰሜንና በሰሜን ምእራብ ባለው የጸጥታ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንቅልፍ እያጣ የመጣው ወያኔ ፣ በቅርቡ በተወሰኑ አካካቢዎች የሚገኙ የሱዳን ድንበሮችን ለመዝጋት ቢሞክርም እንዳልተሳካላት ወታደራዊ ምንጮቻችን ከስፍራው ዘገቡ።

ወያኔ በአካባቢው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙትን ተቃዋሚዎች ለመግታት እና ለሱዳን ከተሰጠው መሬት ጋር በተያያዘ ሊነሳ ይችላል ብሎ የሚፈራውን እንቅስቃሴ ለማፈን በማሰብ ከጥር 3 ቀን 2002 ዓም ጀምሮ ተጨማሪ ወታደራዊ ስምሪት በማድረግ፣ ከሰሜን ምእራብ ጫፍ የሱዳንንና ኤርትራን ድንበሮች ከሚያገናኘው ከአምደይት በር ጀምሮ ወደ ደቡብ ምእራብ አቅጣጫ በመዝለቅ እንዲሁም የአሲራን በር በመዝጋት እስከ ሲናርና መተማ ድንበር ድረስ ያለውን ገዢ መሬት ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢገኝም ፈጽሞ ሊሳካለት እንዳልቻለ ወታደራዊ ምንጮቻችን ዘግበዋል።

አምደይት ከሁመራ በግምት ከ20 ኪ/ሜ ባልበለጠ እርቀት ላይ የምትገኝ የኢትዮጵያ ፣ የኤርትራና የሱዳን ዜጎች በየጊዜው የንግድ ልውውጥ የሚያካሂዱባት የሱዳን ድንበር ከተማ ስትሆን፣ የዚህን በር ለመዝጋት ያነሳሳው ዋናው ምክንያት ጥር አንድ እና ጥር አራት 2002 ዓም የተቃዋሚ ሀይሎች በአምደይት ከተማ በቅርብ እርቀት የምትገኘውን ጀመሪክ ወይም ዲማ የምትባለውን የኢትዮጵያን መለስተኛ ከተማ በማጥቃታቸው መሆኑ ተገልጿል። እንዲሁም ይላሉ ወታደራዊ ምንጮቻችን፣ የወያኔን ዘረኛና ያረጀ አገዛዝ እየከዳ ወደ ተቃዋሚው ጎራ የሚገባው ሰራዊት ብዛት መጨመር እያስጨነቀው በመምጣቱ የድምበር ከተማዋን ለመዝጋት ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት ቀርቶአል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከጀማሪክ ተነስቶ የሉግዲን ተራራ አልፎ እስከ አንገረብና ጓንግ ወንዞች መገናኛ ድረስ ያለውን የአገሪቱን ሰሜናዊ ምእራብ ጫፍ የያዘ መሬት ሙከራ አድርጎ ነበር። ይህ አካባቢ ወያኔ በማሌሊት ማንፌስቶ የቀረጻትን ታላቂዋን ትግራይ ከፖርት ሱዳን ጋር በማገናኘት የአዲሲቷን የትግራይ ሪፖብሊክ የወጪ ንግድ ለማቀላጠፍ ሲባል የጎንደርን መሬት ወደ ትግራይ ያካለለው የመሬት ክፍል መሆኑ ይታወቃል።

ወያኔ በጀማሪክ አካባቢ ቀይ ጨርቅ በማውለብለብ በዚህ ቀይ መስመር ቀጠና የተገኘ ማንኛውም ሰው በጥይት እንዲመታ በአካባቢው ለሚገኘው የመከላከያ ክፍለ ጦር ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም ህዝቡ ግን እንቅስቃሴውን ለመገደብ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመጣስ የተለመደ እንቅስቃሴውን እንደቀጠለ ፣ ሆኖም ለጸበል ወደ ዲማ የሄዱ አንዳንድ ህሙማን በክልሉ በሰፈሩት የወያኔ ወታደሮች በከፍተኛ ሁኔታ መደብደባቸውን ከወታደራዊ ምንጮች ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

ወያኔ ከጀማሪክ በተጨማሪ ከአብድራፊ ከተማ በ31 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘውን የሱዳን ጠረፍከተማ የሆነችውን የአሲራን በር ከጥር 7 ቀን 2002 ዓም ጀምሮ ለመዝጋት ሙከራ ያደረገ ሲሆን፣ በዚሁቀን ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ሰዎችንና እቃዎችን ሲያመላልሱ የነበሩ የሰሌዳ ቁጥራቸው ኮድ 3 ትግራይ 00338፣ ኮድ 3 ትግ 00367፣ ኮድ3 ትግ 01086 እንዲሁም ኮድ 3 አማራ 00287 የሆኑ ሁለት ላንድሮቨሮችና 2 ቶዮታዎች በጦሩ ተይዘው በአብድረፊ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎአል።

የመኪኖቹ ሾፌሮች ታስረው የተፈቱ መሆናቸውን ከነዋሪዎች ያገኘነው መረጃ የሚያመለክት ሲሆን፣ አንድ ስሙን ለጊዜው ያላወቅነው ሰው ደግሞ በከተማይቱ መሀል አደባባይ ላይ ታስሮ ቀኑን ሙሉ በጸሀይ ሀሩር እንዲመታ ከተደረገ በሁዋላ ፣ በወያኔ ጦር ተወስዶ ሳይመለስ መቅረቱን ታምኝ ምንጮቻችን ተናግረዋል።

በተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ እየተደናበረ የመጣው ወያኔ በሰሜን ምእራብ የጠረፍ ከተሞች የሰአት እላፊ አዋጅ ማወጁም ታውቋል። ወያኔ አካባቢዉን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ከጀማሪክ ጫፍ እስከ መተማ ከተማ ድረስ ያለውን የተንጣለለ የኢትዮ -ሱዳን መሬት ለመቆጣጠር እንዳልቻለና ፈጽሞ መቆጣጠር እንደማይችልም ወታደራዊ ምንጮቻችን አክለው ዘግበዋል።

ሰሞኑን የወያኔ ቴሌቪዥን የተቃዋሚ ሀይሎች በድንበር አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የጸጥታ ስጋት እየፈጠሩ ናቸው በማለት መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን፣ እነዚህን ሀይሎችም የይስሙላውን ምርጫውለማደፍረስ፣ ባለስልጣናትን ለመግደል እና ተቋማትን ለማውደም የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች ናቸው በማለት በተዘዋዋሪ መንገድ የችግሩን መኖር ለማመን ተገዷል። ከአንድ ወር በፊት ደግሞ የወያኔ የስለላ ሀላፊ የሆነው ጌታቸው አሰፋ የሱዳን ባለስልጣናትን ወደ መቀሌ በመጥራት በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተቃዋሚ ሀይሎችን ለመግታት ተባበሩን ብሎ ጥያቄማቅረቡ ታውቋል። ወያኔ ህዝባዊ ተቃውሞዎችን ለማፈን የተለያዩ ሙከራዎችን እያደረገ ቢሆንም፣ ቃዋሚዎች የሚያገኙት ህዝባዊ ድጋፍ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ምንም ለማድረግ እንዳልቻለታውቋል። የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን በመስጠቱ ክፉኛ የተበሳጨው እንደሁም ታላቁዋን ትግራይን ለመመስረት በሚል ሰበብ ከጎንደር ግዛቶች እየተቀነሰ ለትግራይ ግዛት በሚሰጠው መሬት ልቡ ያረረው የጠረፍ አካባቢ ህዝብ፣ ለተቃዋሚዎች ድጋፉን አጠናክሮ በመስጠት ላይ መሆኑንም ያገኘነው መረጃ አመልክቷል።

## ወያኔ በለንደን የሚገኘውን የኢትዮጵያን ኢምባሲ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ከዚህ መረጃ ጋር በተያያዘ አንድ ቀደም ብለው የወያኔ ኢሃዴግ አባል የነበሩ ነገር ግን ባሁኑ ሰአት በእንግሊዝ ሃገር በስደት ላይ የሚገኙ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ግለሰብ አስተያየታቸዉን እንዲሰጡን ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡን መልስ መለስና ተከታዮቹ ፍላጎታቸዉ አላማቸውና አካሄዳቸው ምን እንደሆነ ያሳወቁት ዛሬ ሳይሆን ከበርካታ አመታት በፊት ቀደም ብሎ እንደሆነ አውስተው ወያኔ የሰው ልጂን ሳይቀር የሃገሪቱን ለም መሬቶች ተቁዋማት ቅርሶችና ሌሎቹንም ዋጋ ያወጣሉ ብሎ ያመነባቸውን ሁሉ ለሽያጭ ያቀረበ ጨካኝ አገዛዝ መሆኑን ለማያውቁት ካልሆነ በስተቀር ለኔ አይገርመኝም ብለዋል። ይሁን እንጂ ይላሉ አስተያየት ሰጪው፣ ኢትዮጵያዊያን ድንበራችን አንጡራ ሃብታችንን እህቶቻችንንና ህጻናትን ሳይቀር በዚህ ሀገወጥ አገዛዝ የተሸጡ መሆኑን ባይናችን እያየን ለምን ትእግስታችን መሙዋጠጥ እንዳልቻለና አሁንም ከወያኔ ሌላ ጥፋት ለምን ዝም ብለን እንደምንጠብቅ ነው ብለዋል።

## የደደቢት የብድርና ቁጠባ ተቋም ሌላው የወያኔ . . . ከገጽ 1 የዞረ

መንግስታዊ ያልሆኑት ተቋማት የሚል ስም የተሰጣቸው የገበሬዎች የሴቶችና የወጣቶች ማህበራት መሆናቸውን ያጋለጠው ጽሁፉ እንደፈረንጆች አቆጣጠር በ2008 ማለቂያ ላይ ተቋሙ ከ 146 ሚሊዮን ዶላር (ወደ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር) በላይ እንደሚያንቀሳቅስና በንብረትነት የተመዘገበው የሃብት መጠን ደግሞ ከ185 ሚሊዮን ዶላር በላይ ( ወደ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚጠጋ) መሆኑ ታውቋል።

ይህን ተቁዋም በቅርበት የሚያዉቁ ታማኝ ምንጮች ለግንቦት ሰባት በሰጡት አስተያየት ተቋሙ በዋናነት የተቋቋመው በተለይም የዓለም ባንክና አንዳንድ ታላላቅ የሆኑ በብድር አገልግሎት ዙሪያ የሚሰሩ ዓለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጂቶችን የገንዘብ ፈሰስ ለመዋጥ እንደሆነ ገልጸው፤ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች የተቋቋሙት የብድርና የቁጠባ ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግን አቅማቸው ደካማ የሚሰጡትም አገልግሎት እጂግ አናሳ መሆኑን አስረድተዋል። በተለይም ይላሉ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች፤ በጣም የሚገርመውና ለማንም ይፋ ያልሆነው፣ የዚህ የብድር ተቋም ሚስጥራዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ መጠን ያለው ከለጋሽ ሃገራት ለብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ በቁጥጥሩ ስር በማዋል፣ ተመሳሳይ ተቋማት በሌሎች ክልሎች ባሉበት ሁኔታ፣ የደደቢቱ ተቋም ወደ ሌሎች ክልሎች በመሄድ ገንዘብ የማጋበሱን ስራ እንዲፈጽም መደረጉ ነው ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ400 በላይ የሚሆኑ የቻይና ዜግነት ያላቸው የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሰራተኞች ላለፉት ሁለት ሳምንታት የስራ ማቆም አድማ በመምታታቸው ምክንያት በተፈጠረ ግጪት በርካታ ሰዎች የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው የተገለጸ ሲሆን ለዚሁ የስራ ማቆም አድማና ግጭት መነሻ የሆነው ለቻይናዊያን ሰራተኞቹ በቀጥታ ከሚከፈላቸው 800 ብር ክፍያ ዉጪ ያለው ደመወዛቸው በግል የባንክ አካውንት ቁጥራቸው ሊቀመጥላቸው ስምምነት ላይ ተደርሶ የነበረ ቢሆንም ከሶስት ወራት በላይ በሚሆን ጊዜ ዉስጥ ምንም አይነት ገንዘብ ያልተቀመጠላቸው መሆኑን ካረጋገጡ በሁዋላ መሆኑን ለማወቅ ተቿሏል። የዜና ምንጫችን የተፈጠረዉን ችግር አስመልክቶ ባደረገው የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ለዚህ ሁሉ ችግሮች መፈጠር ከበስተጀርባ እንደ ኤፈርትና ደደቢት ያሉ ተቋማት የሃገሪቱን ባንኮች አንጡራ ሃብት ያለምንም ሃይ ባይ እየዘረፉ የመሆናቸው እዉነታ ነው ብሎአል።

በሌላም በኩል ባሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ እየተስፋፋ ያለው ፍጹም ህገወጥ የሆነ የባንክ ዘረፋ ሃገሪቱን ወደባሰ አዘቅት ይዙዋት እየወደቀ መሆኑን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ገልጿል። ዘጋቢያችን እንደገለጸው የወያኔው አገዛዝ በስልጣን ላይ ያሉት ወንበዴዎች እያንዳንዳቸው ከሚያደርጉት ዘረፋ በተጨማሪ በተለያዩ አቅጣጫዎች እየተደረገ ያለው ልቅ የሆነ የአደባባይ ላይ ዝርፊያ አሁንም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ህይወትን ቁልቁል እያወረደው መሆኑን አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ኑዋሪዎች መግለጻቸዉን ዘግቧል። ነዋሪዎቹ እንዳሉት የወያኔው አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር ባለው ሚዲያ ያለምንም ተቀናቃኝና ጠያቂ የኢኮኖሚ አቅማችን አደገ ተመነደገ ይበል እንጂ በተጨባጭ እየታየ ያለው አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮዉን በሰቆቃ እየገፋ ባንጻሩ ደግሞ እጂግ በጣት የሚቆጠሩ የአገዛዙ ባለስልጣኖችና ቡቺሎቻቸው የተንደላቀቀ ኑሮ እየኖሩ መሆኑን ገልጸዋል። ነዋሪዎቹ ለሰጡት ማብራሪያ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ ገንዘብ ዋጋ አሁንም መውደቁንና ባሁኑ ሰአት በሚገርም ሁኔታ በህጋዊ ባንኮች የአንድ ዶላር ምንዛሪ ብር 13. 60 መድረሱን በጥቁር ገባያ ደግሞ እስከ 17 ብር በመሸጥ ላይ መሆኑን አስታውሰዋል።

የኢትዮጵያ ብር ከመስከረም 2001 ወዲህ ባለው ጊዜ ብቻ ዋጋዉን ሲያወርድ ይህ ለአራተኛ ጊዜ መሆኑ ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661